## የቤት ኪራይ እርዳታ ይፈልጋሉ?

የኪንግ ካውንቲ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው እንዳይባረሩ የመርዳት እና የኪራይ ድጋፍ መርሃ (EPRAP) በCOVID-19 ችግሮች ምክንያት የቤት ኪራያቸውን ሳይከፍሉ ለዘገዩ ነዋሪዎች ለኪራይ እና ለአገልግሎት ክፍያዎች እገዛ ያደርጋል።

**ኪንግ ካውንቲ ከፌብሩዋሪ 28፣ 2022 በኋላ የኪራይ እገዛን በተመለከተ አዲስ ማመልከቻዎችን አይቀበልም።**

እባክዎን በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የኪራይ እገዛ እያደረጉ ካሉ ኤጀንሲዎች ጋር ለመገናኘት 211 ይደውሉ።

## አስቀድሜ ተመዝግቤስ ከሆነስ?

ከፌብሩዋሪ 28፣ 2022 በፊት በድረ-ገፃችን በተከራይ መግቢያ (ፖርታል) በኩል ለኪንግ ካውንቲ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው እንዳይባረሩ የመርዳት እና የኪራይ ድጋፍ መርሃ (EPRAP) ላይ ተመዘግበው ከነበረ፣ ከተሰበሰቡት የተከራይ ማመልከቻዎች ውስጥ አሁንም እርዳታ ለማግኘት የመመረጥ እድል አለዎት። ኪንግ ካውንቲ በፕሮግራሙ ለመሳተፍ የተመዘገቡ ተከራዮችን ከተከራይ ፖርታሉ ላይ በየሳምንቱ ይመርጣል። የተመራጩ ቁጥር እንደ አገልግሎት አቅራቢዎቹ አቅም ይለያያል። አስቀድመው የተመዘገቡ አመልካቾች የማመልከቻቸውን አሁናዊ ሁኔታ ወደ ተከራይ የድርገፅ መግቢያ (ፖርታል) ላይ ገብተው ማየት ይችላሉ።

**የኪንግ ካውንቲ (EPRAP) የገንዘብ አቅም የተወሰነ ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ የተመዘገቡትን ሁሉ መርዳት አንችልም።**

እርስዎን ማግኘታችንን እንቀጥላለን ፤ የደረስንበትንም እናሳውቆታለን። ለእርዳታ ከተመረጡት ቤተሰቦች አንዱ ሊሆኑ ስለሚችሉ እባክዎ ኢሜልዎን ይመልከቱ ፤ በተጨማሪም ከማያውቁት የስልክ ቁጥሮች የሚመጡ የስልክ ጥሪዎችን እና የጽሁፍ መልክቶችን አንብበው ይመልሱ።

## የ(EPRAP) ክፍያ ውል ምንድን ነው?

ከኪንግ ካውንቲ ሰዎች ከመኖሪያ ቤታቸው እንዳይባረሩ የመርዳት እና የኪራይ ድጋፍ መርሃ (EPRAP) የቤት ኪራይ ክፍያ ለመቀበል፣ የቤት አከራዮች የEPRAP ክፍያ ውልን (እንዲሁም T-RAP ቅጽ የሚባለውን) ፈርሟል። ይህ ውል (ሰነድ) EPRAP የቤት ኪራዮችን ስለከፈለባቸው ወራት (የክፍያ ጊዜ) እና አከራዮች የተስማማባቸውን ውሎች እና ሁኔታ መረጃን ያካትታል። ይህ መረጃ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካትታል፡

- የክፍያ ጊዜው ካለቀ በኋላ ለ6 ወራት የቤት ኪራይ ላለመጨመር ወይም ከቤት ላለማስወጣት
- በክፍያ ወራቶቹ ውስጥ ዘግይቶ በሚፈጸሙ ክፍያዎች ላይ ቅጣት ወይም ተጨማሪ ክፍያ ላለማድረግ

**የቤት አከራዮች የፈረመውን ውል በEPRAP የድርገፅ መግቢያ (ፖርታል) እዚህ ላይ ማግኘት ይችላሉ።**

እነዚህን ሰነዶች ለማግኘት ተጨማሪ እገዛ ከፈለጉ፣ በዚህ አድራሻ https://bit.ly/RentHelpSupport ኢሜይል ሊያደርጉ ወይም በ (253) 237-2485 ሊደውሉ ይችላሉ።

## ከቤት ማስወጣት ወይም መባረርን በተመለከተ የህግ ድጋፍ ይፈልጋሉ?

በተከራይ ፖርታሉ ላይ የቤት ኪራይ እርዳታን እየጠበቁ ከሆነ ወይም በአሁኑ ጊዜ የቤት አከራዮት ከቤት እንዲለቁ የሚጠይቅ ማስታወቂያ ከሰጦት እርዳታ አለ።

**ቤቶትን ለቀው ለመውጣት ውሳኔ ከማድረግዎ በፊት ወይም ለክፍያ እቅድ ከመስማማትዎ በፊት፣** ስለመብቶት እና የማስወጣት ሂደቱ እንዴት እንደሚሰራ በwashingtonlawhelp.org ይበልጥ መረጃ ያግኙ።

ስለ **የተከራዮች መብት** ጥያቄዎች እና አጠቃላይ መረጃ፣ ለሶሊድ ግራውንድ (Solid Ground's) የተከራይ አገልገሎት የስልክ መልእክት መስመር ላይ በ206-694-6767 ወይም በዋሽንግተን ስቴት የተከራዮች ህብረት የስልክ መስመር ላይ በ206-723-0500 ይደውሉ ወይም https://tenantsunion.org/ ድህረገፅ ላይ ይሞክሩ።

በሲያትል ውስጥ የ"**ክፈል ወይም ልቀቅ" የሚል ማስታወቂያ** ከደረሶት፣ ትክክለኛ ማስታወቂያ መሆኑን ለማረጋገጥ የከተማው ኪራይ ቢሮ የእርዳታ መስመር ላይ በ206-684-5700 ደውለው ያረጋግጡ። በተጨማሪም፣ የኢስትሳይድ (Eastside) የህግ ድጋፍ መርሃ ለተከራዮች የህግ ድጋፍ መስጠት ይችላል። በድህረገፃቸው ላይ ያመልክቱ ወይም በእርዳታ መስመሮቻቸው ላይ ይደውሉ፡ 425-747-7274 (እንግሊዝኛ) 425-620-2778 (ስፓኒሽ)። በተጨማሪም፣ ተከራዮች የተከራይ የህግ ማእከል ላይ በ 206-324-6890 ደውለው እርዳታ መጠየቅ ይችላሉ።

ኪንግ ካውንቲ ውስጥ **የመልቀቂያ መጥሪያ** ከደረሶት፣ የቤቶች ፍትህ ፕሮጀክትን በስልክ ቁጥር 206-267-7069 ወይም በ hjpstaff@kcba.org ኢሜል ያግኙ። ከፍተኛ ያአገልግሎት እርዳታ ጥያቄ ስላለ፣ **የቤቶች ፍትህ ፕሮጀክት በአሁኑ ጊዜ በመፈናቀል ሂደት ላይ የመጀመሪያው ደረጃ ውስጥ ያሉ ተከራዮችን ወዲያውኑ ሊረዳቸው አይችልም**፣ ለምሳሌ የ14 ቀን ማስታወቂያ ለደረሳቸው ተካራዩች።

[1]

[1] 745_COV Amharic_TenantEvictionPreventionFact_Sheet 04212022